# ከ ኦስትሪያ ቅንጅት ድጋፍ አስተባባሪ ቻፕተር የተሰጠ መግለጫ !

## የቅንጅት ግብ አምባገነኖችን አስወግዶ በአምባገነኖች ለመተካት አይደለም !

ከሁሉ አስቀድመን በቅርቡ በቅንጅት ከፍተኛ አመራር ላይ አቶ ኃይሉ ሻወል የወሰዱት ኢዲሞክራሲያዊና አምባገነናዊ ውሳኔ ፍጹም ተቀባይነት የሌለውና ይልቁንም ከቅንጅት መሰረታዊ ዓላማና ከፓርቲው አሰራር መርሆዎች እጅጉን ተጻራሪ በመሆኑ ቅሬታችንን እያሳወቅን አቶ ኃይሉ ሻወል የበደሉትን የኢትዮጵያን ህዝብና እምነቱን የጣለባቸውን ብርቅ የቅንጅት ከፍተኛ አመራር አባላትን ዛሬ ነገ ሳይሉ ባስቸኳይ ይቅርታ ይጠይቁ ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ቅንጅትን ቅንጅት ያሰኙትና የህዝብን መልካም ፈቃድ እንዲያገኝ ያደረገው የቀመለት ራዕይ እና የኢትዮጵያ ህዝብ የለውጥ ፍላጎቱ በታሪክ አጋጣሚ ስለተገጣጠሙ ነው። የህዝቡ ኢኮኖሚያዊ ድቀት፣ ዲሞክራሲያዊ እጦትና በአገሪቱ የናኘው የፍትህ ጉድለት በአጠቃላይ የሰባዊ መብት ረገጣው የህዝብ ጫንቃ መሸከም ከማይችልበት ደረጃ መድረሱን በምርጫ 97 በስልጣን ላይ ላለው መንግስት በገሃድ አሳውቋል። በምርጫው ውጤትም ያስተዳድሩኛል ያላቸውን መሪዎቹን በመምረጥ ለአዲስ የፖለቲካ ስሪት መዘጋጀቱን አረጋግጧል። ይህ በእንዲህ እያለ ነው የምርጫው ውጤት ያስደነገጠው ወያኔ ኢህአዴግ የህዝብን ድምጽ በጸራራ ጸሃይ የሰረቀው። ይህ በሆነ በማግስቱ ህዝቡ ድምጹ እንዲከበርለትና የተጀመረው ዲሞክራሲያዊ አካሄድ ይቀጥል ዘንድ ተቃውሞውን በሰላማዊ መንገድ ከዳር እንከዳር አስተጋባ። በአንጻሩ ግን ወያኔ ኢህአዴግ የህዝቡን ቅስም በመስበር ብቅ ብላ የነበረችውን የዴሞክራሲ ጭላንጭል ደምጥጦ ሰላማዊውን ህዝብ በግፍ ጨፈጨፈ በሺዎች የሚቆጠሩትንም በየበረሃው በሚገኙ እስር ቤቶቹ አጉሮ አሰቃየ ይብስ ብሎም ህዝብ የመረጣቸውን መሪዎች እስር ቤት እንዲማቅቁ አደረገ።

ባጭሩ የወያኔ ኢህአዴግ ፍላጎትና አላማ ህዝቡን በማሰርና በመግደል መሪዎቹንም ዘብጥያ አውርዶ ምንም አይነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ በማድረግ እና በአጠቃላይ በአገሪቱ ዳር እስከ ዳር ሽብር በመልቀቅ የቅንጅት ራዕይ በተስፋ ብቻ እንዲገታ ለማድረግ ነበር። ይህን የተረዱ የቅንጅት መሪዎች ትግሉ እንዳይቆም ቢያንስ ፖለቲካው በስደት አገሮች በተደራጀ መልኩ እንዲቀጥል የቅንጅት አለም አቀፍ አመራር እንዲመሰረትና በስሩ በየአገሩ የድጋፍ ድርጅቶችን በማቋቋም በፋይናንስ በዲፕሎማሲና በፕሮፓጋንዳ ትግሉ እንዲካሄድ ሃላፊነቱን ሰጡ።

ታድያ ይህ ሁሉ በሚሆንበት ጊዜ በአለም አቀፍ አመራሩ ውስጥ ቅራኔዎች እየተፈጠሩና አምባገነናዊ ውሳኔዎችም በአመራሩ ሊቀመንበር በሻለቃ ዮሴፍ መተላለፍ ጀመሩ። በወቅቱ ይህ አካሄድ ቅንጅት ከቆመለት ጽንሰ ሃሳብ ተጻራሪ በመሆኑና ፓርቲውን አደጋ ላይ እንደሚጥል በማመን የድጋፍ ድርጅቶች በሙሉ ተቃውሞአቸውን በሻለቃው ላይ ሰነዘሩ። ሆኖም ከነሻለቃ በኩል የሚሰጠው መልስ ትእዛዙ ቀጥታ ከቃሊቲ ከአቶ ኃይሉ ሻወል እንደሚመጣ በተደጋጋሚ ሲናገሩ ስንሰማ ለማመን እንቸገር ነበር። ሆኖም እየዋለ እያደረ የተለየዩ አምባገነናዊ ትዕዛዞች በሊቀመንበሩ በአቶ ኃይሉ ሻወል እጅ እየተጻፉ ከእስር ቤት ሾልከው መድረስ ጀመሩ። በርግጥ አብዛኞቻችን በሊቀመንበሩ ላይ ያለን እምነት ከዕለት ወደ ዕለት እየመነመነ መምጣቱን ባንናገረውም ግልጽ ነበር። ከእስር ቤት የመፈቻቸው ተስፋ እየጎላ በመጣ ቁጥር በአለም አቀፉ አመራር ውስጥ ለተፈጠረው ችግር መንስኤው ይጣራል መፍትሄውም ይገኛል የሚል ተስፋ አዝለን የሚፈቱባትን ቀን በጉጉት ጠበቅን። ዳሩ ምን ያደርጋል የሚፈቱበት ቀን ሊደርስ ትንሽ ቀናት ሲቀሩ በአቶ ኃይሉ ሻወል አምባገነናዊ ትዕዛዝ ሁለት አስታራቂ ተብየ ሽማግሌዎች ተልከው አለም አቀፍ አመራሩን አፍርሰው በምትኩ አለም አቀፍ

ካውንስል የሚባል አቋማቸው ጸረ ቅንጅት መሆናቸውን በራሳቸው አንደበት ሲገልጹ በነበሩ እንደ ዶ/ር ታየ ባሉ ሰወች የሚመራ ድርጅት እንዲቋቋም ተደረገ። አሁንም ተስፋ ባለመቁረጥ መሪዎቹ ሲፈቱ ችግሩ አብሮ ይፈታል በሚል አጉል ተስፋ ጠበቅን።
በመጨረሻም መሪዎቹ ተፈቱ። በውጭም ሆነ በአገር ቤት የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ደስታውን አበሰረ። አዲስ ተስፋም ፈነጠቀ። ሆኖም እውነት ታፍና አትቀርምና አቶ ኃይሉ እስር ቤት ሆነው ሲጠነስሱት የነበር ተንኮል በገሃድ ይወጣ ጀመር። በአመራሩ ላይ ለተከሰተው ክፍተት ዋናው መንስዔ እራሳቸው ሊቀመንበሩ መሆናቸውን ያለምንም ሃፍረት በድፍረት መናገር ጀመሩ። ይባስ ብለውም ጎራ ለይተው ብጤዎቻቸውን አሰባስበው ቅንጅትን የመበታተን ሴራ በይፋ ተያያዙት። ዳሩ የረባ ድጋፍ በማጣታቸውና ተስፋ በመቁረጣቸው ያልሞት ባይ ተጋዳይ አስቂኝ ውሳኔያቸውን ህዝብ በሚወዳቸው ብርቅየ የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ከፍተኛ አመራር አባላት ላይ ወሰኑ።

በመሆኑም በኦስትሪያ የቅንጅት ድጋፍ አስተባባሪ ቻፕተር፤

1) አቶ ኃይሉ ሻወል የኢትዮጵያ ህዝብ ራዕይ የሆነውን ቅንጅትን ለማዳከምና ለመበተን የሚፈጽሙት ወንጀል አይደለም ከአንድ መሪ ከተራ አባል እንኳ የማይጠበቅ በመሆኑ ከልብ ያዘን መሆናችንን እየገለጽን ለጥፋታቸው ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት የላዕላይ ምክር ቤቱ ይወስን ዘንድ እንጠይቃለን።

2)አቶ ኃይሉ ሻወል ቀደም ሲል ያከናወኗቸውን አመራሮችን ስንመረምር ብቃታቸው አጠያያቂ በመሆኑና ቅንጅትን የሚያክል ግዙፍ የፖለቲካ ድርጅት ለመምራትም የመንፈስ ብቻ ሳይሆን የአካል ጥንካሬም አስፈላጊነቱ እሙን በመሆኑ በምትካቸው ለቦታው ተመጣጣኝ የሆነ ሰው ላዕላይ ምክር ቤቱ መርጦ ርሳቸውን እንዲያሰናብት እንጠይቃለን።

3) በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በአቶ ኃይሉ ሻወል የጥፋት ተልዕኮ ስር በመንቀሳቀስ ላይ ያላችሁ እና አሁንም ለኢትዮጵያ ህዝብ የፖለቲካ ህይወት ቅንጅት የተሻለ አማራጭ ነው የምትሉ ሁሉ ወደ ትግሉ ጎራ ትመለሱ ዘንድ እንጠይቃለን

ቅንጅት የህዝብ እንጂ የአምባገነኖች አይደለም !

ድል ለ ኢትዮጵያ ህዝብ !